ኩባንያችን መስፍን ብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኃላ.የተወ.የግል ማህበር (FSWE ኢንድስትሪ) ከታች በሰንጠረዡ የተገለፁትን የተለያዩ መጠን ያላቸው የፋብሪካ ግብኣቶች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ስለሚፈልግ

የተለቀቀበት ቀን: ሓሙስ ሕዳር 25, 2018 (ከ 3 ወር)
መዝግያ ቀን: ሓሙስ ታሕሳስ 9, 2018 04:00 ጥዋት (ተዘጋ)
የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:በየ ሎቱ ይለያያል
ቦታ:መቐለ
የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:200
ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ሓሙስ ታሕሳስ 9, 2018 04:30 ጥዋት
ምድብ: ኮንስትራክሽን ማሽነሪን ኣቁሑትን/ ኤሌክትሪካልን መሳርሕታትን መለዋወጢን/ ኤሌክትሮ-መካኒክስ ኣቁሑትን ግልጋሎትን/ ቱቦታትን ኣክሰሰሪታትን/

የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

ኩባንያችን መስፍን ብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኃላ.የተወ.የግል ማህበር (FSWE ኢንድስትሪ) ከታች በሰንጠረዡ የተገለፁትን የተለያዩ መጠን ያላቸው የፋብሪካ ግብኣቶች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ስለሚፈልግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የምታሟሉ ተወዳዳሪዎች እንድትሳተፉ ድርጅታችን ይጋብዛል::

በጨረታ የሚገዙ ግብኣቶች ዝርዝር

Lot-01

ተ.ቁ	የዕቃው ዓይነት ዝርዝር	>መለኪያ	ብዛት	ማብራርያ
01	Sheet Metal 2500*1000*2mm, st-37	Pcs	592	
02	Sheet Metal 2500*1250*2mm,st-37	Pcs	105	
03	Pipe,Bronze Ext 056*int035*110mm	Pcs	66	
04	Round Rod,steel Ø30*6000mm,st-37	Pcs	09	
05	Round Rod,steel 025*6000mm,st-37	Pcs	02	
06	Round Rod,steel 20*6000mm st-37	Pcs	75	

Lot-02

ተ.ቁ	የዕቃው ዓይነት ዝርዝር	>መለኪያ	ብዛት	ማብራርያ
01	Brake System for 3-Axle draw bar	Set	06	
02	Deep stick,3Meter length width	Pcs	32	
03	Steel Cable Ø12mm	M	4,000	
04	Steel Cable 8*8mm	M	156	
05	Silicon Sealant	Pcs	115	
06	Wire, Steel welding 04mm for submerged arc welding	Roll	120	1 Roll 25kg
07	Welding Wire 1.2mm	Roll	221	1 Roll 15kg
08	Elbow PVC 110mm, 45 degree	Pcs	227	
09	Self Screw Drill 5.5 * 55mm	Pcs	12,226	

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle

የጨረታው መስፈርት

1. ተጫራቾች በዘርፉ የ2018 ዓ/ም የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ ፣ የግብር

ከፋይ መለያ ቁጥር እና የጥቅምት ወር ቫት ማሳወቅያ ሰነድ ፎቶ ኮፒ በማያያዝ ከጨረታው ዝርዝር (ሰነድ) ጋር ማስገባት ይኖርባቸዋል::

2. ተጫራቾች የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የጥቅምት ወር ሻት ማሳወቅያ

የማይመለስ ፎቶ ኮፒ ሰነድ እና የሚመለስ ኦርጅናል በመያዝ የጨረታ ሰነድ ከ 04/12/2025 እ.ኤ.አ ጀምሮ እስከ 18/12/2025 እ.ኤ.አ መቐለ ላጪ ቅርንጫፍ FSWE ኢንድስትሪ በስራ ሰኣት የማይመለስ 200 ብር(ሁለት መቶ ብር) በመክፈል እና ለናሙና የቀረበ ንብረት በማየት የጨረታ ሰነድ መውሰድ ይኖርባቸዋል::

3. ተጫራቶች የተሟላ የጨረታ ሰነድ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን መቐለ ላጪ ቅርንጫፍ FSWE ኢንድስትሪ ጨረታ ከወጣበት ቀን ጀሚሮ እስከ 18/12/2025 እ.ኤ.አ ከጥዋቱ 4:00 ሰዓት ማስገባት ኣለባችው::

4. ጨረታው በ18/12/2025 እ.ኤ.አ ከጥዋቱ 4:00 ሰዓት ተዘግቶ በተመሳሳይ ቀን 4:30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት መቐለ ላጪ ቅርንጫፍ FSWE ኢንድ ቢሮ የሚከፈት ሲሆን ሰነዳቸው የተሟላ ከሆነ ባይገኙም የጨረታ ሰነዱ ይከፈታል::

5. ተጫራቾች የሚያስገቡት ዋጋ ጨምሮ መሆኑና አለመሆኑን በግልፅ መጥቀስ አለባቸው:: ይህ ካልሆነ ግን ያስገቡት ዋጋ ቫት እንደሚያካትት ተቆጥሮ ይወሰዳል::

6. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ ክፍያ ማዘዣ (ሲፒኦ) ለ lot -01 ብር 150,000.00 (ኣንድ መቶ ኣምሳ ሺህ ብር) እንዲሁም ለ lot -02 ብር 100,000.00 (ኣንድ መቶ ሺህ ብር) በታሸገ ፖስታ ከጨረታው ጋር ማስገባት አለባቸው::በፖስታ ያልታሸገ ሲፒኦ ተቀባይነት የለውም::

7. አሸናፊ ተጫራቾች ጨረታውን ማሸነፋቸው የግዥ ማዘዣ ከደረሳቸው ቀን ጀምሮ ያቀረቡትን ናሙና ተቀባይነት ካገኘ በኋላ በ5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የጠቅላላ ዋጋ ቫት ጨምሮ 10% የውል ማስከበርያ የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) በማሰራት ከኩባንያችን ጋር ውል መፈራረም አለባቸው:: ይህ ካልሆነ ግን ለጨረታ ማስከበርያ ያስያዙት ብር ለድርጅቱ ገቢ ሆኖ ድርጅቱ ሌላ አማራጭ ይወስዳል::

8. አሸናፊ ተጫራቾች ጨረታውን አሸንፈው ውል ካሰሩበት ቀን ጀምሮ በ 5 (ኣስራ ኣምስት) ተከታታይ ቀናት ውስጥ እቃው ማስረከብ አለባቸው:: ይህ ካልሆነ ግን ለውል ማስከበርያ ያስያዙት ብር ለድርጅቱ ገቢ ሆኖ ድርጅቱ ሌላ አማራጭ ይወስዳል::

9. ተጫራቾች በሌላ ተጫራቾች ዋጋ ተመስርተው ዋጋ ማስገባት አይፈቀድም፤ እንዲሁም በቅድመ ሁኔታ የተመሰረተ ዋጋ ተቀባይነት የለውም፤ በተጨማሪም ስርዝ ድልዝ እና የተጫራቶች የስልት ስህተት ያለበት የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም::

10. ተጫራቾች ይህን ጨረታ ካሸነፉ ለሌላ ሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት አይችሉም::

11. ተጫራቾች ተጫርተው ያሸነፉት እቃ መቐለ ዋና መስርያ ቤት ድረስ መጥተው ማስረከብ አለባቸው:: ክፍያ በተመለከተ ያቀረቡት እቃ ድርጅታችን ጥራት ቁጥጥር ባለሙያ ተፈትሾ ተቀባይነት ካገኘ በኃላ በ7 ቀናት ውስጥ የሚፈፀም ይሆናል::

12. ኩባንያው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው::

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle